*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

የካቲት 9 ቀን 2003 ዓ.ም

# የደስታ መግለጫ

በተለያዩ የዓለም አካባቢዎች የሚገኙ ሕዝቦች ለሰላም መጎናፀፍ፡ ለሰብዓዊና ለዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው መከበር ለሚያደርጉት ትግል አጋር የሆነውና በሀገራችንም ሳያሰለስል በፅናት የሚታገለው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የቱኒዚያና የግብፅ ሕዝብ ላለፉት 20ና 30 ዓመታት በልዩ ሁኔታ ከጫንቃዎቻቸው ላይ ተቆናጠው ሲበድሏቸው ሲያሰቃዩዋቸውና ሲገድሏቸው፤ ለስየልና ለስደት ሲዳርጓቸው በነበሩት አምባገነኖች ቤን አሊና ሆስኒ ሙባረክና አገዛዞቻቸው ላይ የመጀመሪያውን ድል በመቀዳጀታቸው የተሰማውን ደስታ ይገልፃል። ይህ የመጀመሪያ ድላቸው ለሚቀጥለው ትግላቸው ወሳኝ በመሆኑ፣ አጥብቀው የታገሉለትም ነውና የቱኒዚያና የግብፅ ሕዝብ በጠቅላላ በትላልቅ ከተሞች ብቻ ሳይሆን በገጠሩም በነቂስ ወጥተው የተሰማቸውን ከፍተኛ ደስታ መግለጻቸው የሚያስገርም አይሆንም። ኢሕአፓም ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ የደስታችሁ ተካፋይ ናቸውና እንኳን ደስ አላችሁ ይላሉ።

የቱኒዚያው የለውጥ እንቅስቃሴና በአምባገነኑ ቤን አሊ ላይ ድልን መቀዳጀት ለግብፅ ለውጥ ፈላጊዎችና ግንባር ቀደም ታጋዮች ውስጣዊ ግፊት እንደሰጣቸሁ ሁሉ እንቅስቃሴያችሁም በነዚህ 18 ቀናት ስኬት ማግኘቱ በተመሳሳይ መልክ ለሚገኙ አካባቢዎችና አፍሪካዊያን ታጋዮች የሚሰጠው መልዕክት የተለየ ሊሆን አይችልም። ይህ ድላችሁ የተገኘው በቆራጥነት፣ በፅናትና በአንድነት ታግላችሁ በየሀገሮቻችሁ በርካታ ዜጎቻችሁንም በመስዋዕትነት ገብራችሁ ነውና ታላቅ አድናቆትን ከሰላም ወዳድ ኃይሎች አትርፎላችኋል። የሚከበር፣ የሚደነቅ የሚታገል ሕዝብ

ብቻ መሆኑን በትግላችሁ አረጋግጣችኋል። በተለይም የወደፊቱን የቱኒዚያንና የግብጽን ዕጣና ዕድል ተረካቢ የሆነው ወጣቱ ትውልድ ለለውጥ ያሳየው ፅኑ ፍላጎት፣ ተነሳሽነትና ትግል አቀጣጣይነት የሚያስደንቅ ብቻ ሳይሆን ለቱኒዚያና ለግብፅ ሕዝብ ኩራትና ክብርን በማጎናጸፉ በታሪክ ማሕደር አሻራውን አስፍሯል። ጥሎበታል። በታሪካችሁ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ከፍታችኋል። በተለይም ውስጣዊ ልዩነቶችን በማቻቻል የፖለቲካ መስመርና የኃይማኖት ልዩነቶችን ወደጎን በማድረግ የሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል አባላትን ያሳተፈ፤ በሚያስተባብሩ የነፃነት ጥያቄና እምባገነን ቤን አሊንና ሙባራክን በማስውገድ ላይ ያተኮረ ትግል በማድረጋቸሁ የተገኘ ድል በመሆኑ፣ ከፍተኛ አድናቆትን ቸሯችኋል።

በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የቆየ ግንኙነት ያለና በተፈጥሮም አባይ ወንዝ ይህን ያህል ከሚባል ቁጥር ለላቀ ዘመን ያቆራኛቸው ሕዝቦች ናቸው። ባሁኑ ጊዜ ከግብፅ ሕዝብ በከፋ ደረጃ በፀረ ሕዝብና ዘረኛው እምባገነን የመለስ አገዛዝ እየተበደለ፣ በመብት አልባነትና በመልካም አስተዳደር እጦት ክፉኛ እየተሰቃየ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ላለፉት 18 ቀናት ያደረጋችሁትን ትግል በጥሞና ሲከታተል መቆየቱ ይታወቃል። በትግላችሁ የትግላችሁ ኢላማ የነበረው ሆስኒ ሙባረክ ከሥልጣን መወገድ ዕውን መሆን ከኢትዮጵያ ጠላቶች በስተቀር ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ደስተኛ ለመሆኑ ምንም አይነት ጥርጥር የለውም።

የኢትዮጵያ ህዝብ በተመሳሳይ መልኩ በየካቲት 66 አንድነቱን ጠብቆና በቆራጥነት ታግሎ የዘውድ አገዛዝን ከጫንቃው ቢያሽቀነጥርም የትግሉን



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ፍሬ ምርጥ ነን በሚሉ የወታደር አምባገነኖች ተነጥቆ ለመከራና ስቃይ ተዳርጎ ዓመታትን ቆጥሯል። እንደገና በትግሉ ወታደራዊ አምባገነኑን ሥርዓት የጣለ ቢሆንም እሱን የተካው የወያኔ አምባገነን ዘረኛ ቡድን ደግሞ ካለፈው በባሰ ሁኔታ በሕዝባችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰበት ይገኛል። ይህንን ዘረኛና አምባገነን የመለስ አገዛዝ ከሥልጣን ለማስወገድ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የናንተ ድል መቀዳጀት ደስታው መሆኑን በመግለፅ ሀገር ወዳዱና ለሕዝብ ቀናኢ የሆነው ታጋይ ክፍል - ግልባጭ በማድረግ ሳይሆን -ተመክሯችሁን ከግንዛቤ በመውሰድ ተመሳሳይ ድል የሚያገኙበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም። ያኔ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የሚኖረው ግንኙነት በጋራ ጥቅሞች ላይ የተመሠረተ ሊሆን የሚችል በመሆኑ የጠነከረና በአካባቢው በተለይም በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መልካም የጉርብትና ግንኙነት እንዲፈጠር ዋና ምሶሶ እንደሚሆን እርግጠኞች ነን።

መልካም ደስታና ድል ለቱኒዚያና ለግብጽ ሕዝብ!!

የኢትዮጵያ ሕዝብም በትግሉ ድልን ይቀዳጃል!!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France